# ለጽንስ ማስወረድ አሠራር ሂደት - በመድሃኒት

## ሆን ተብሎ እያወቁ ጽንሱን ለማቋረጥ ከፈለጉ በመድሃኒት ጽንስን ማስወረድ አንደኛው መንገድ ነው

የመጀመሪያው እርምጃ ከሀኪም ጋር የህክምና ምክር ለማካሄድ ቀጠሮ ማቀናጀት ነው። እንዲሁም ነርስም ተሳታፊ ሊሆን ይችላል። በዚህ የምክር ጊዜ ላይ የጤና ባለሙያ/ዎች የሚያደርጉት:

- ይህ የአሠራር ሂደት ለርስዎ የሚስማማ ከሆነ ማሳወቅ
- በመድሃኒት ጽንስን ስለማስወገድ አሠራር ሂደቱን  መግለጽ
- በቤትዎ ውስጥ ድጋፍ እንዲያገኙ ስለሚደረግ ቅንጅት መወያየት
- በሂደቱ መሄድ ከወሰኑ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ፤ እንዲሁም የሚያስፈልግዎትን መድሃኒት ማዘዣ ያካተተ
- በስምምነት መስጫ ቅጽ ላይ እንዲፈርሙ መስጠት።

በዚህ ወይም በሌላ ቀጠሮ ላይ አልትራሳውንድ እና የደም ምርመራ ሊያደርጉ ይችላሉ።

በመድሃኒት ማስወረዱ ላይ የሚቀጥሉበት ከሆነ፤ የአሠራር ሂደቱ እንደሚከተለው ይሆናል:

- የመጀመሪያውን ኪኒን (ሚፈፕሪስቶን/mifepristone)፤ በኪሊኒክ ወይም በቤት ውስጥ መውሰድ። ሚፈፕሪስቶን/Mifepristone (ቀደም ሲል RU486 በሚል ይታወቃል) ይህም ለእርግዝና የሚረዳን ሆርሞን (ፕሮገስተሮነ/progesterone) ተግባር በማገድ ጽንሱ እንዲቆም ያደርጋል።
- ሁለተኛውን ክኒን (ሚሶፕሮስቶል/misoprostol) ከ24 እስከ 48 ሰዓታት ጊዜ በኋላ (በአብዛኛው በቤት ውስጥ) ይወስዳሉ። ሚሶፕሮስቶል/Misoprostol የማህጸን ጫፍ እንዲለሰልስ እና ማህጸን እንዲኮማተር በማድረግ ጽንሱ እንዲወጣ ያደርጋል።
- ብዙጊዜ ጽንስ ማስወረዱ የሚጠናቀቀው የሁለተኛ ክኒን (ሚሶፕሮስቶል/misoprostol) ከወሰዱ በኋላ ከአራት እስከ ስድስት ሰዓታት ባለው ጊዜ ነው። ከዚያም በላይ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።
- በአብዛኛው የአንድ ወይም የሁለት ቀን እረፍት ወይም እንቅስቃሴን መቀነስ ይኖርብዎታል።

## የጽንስ ማስወረጃ መድሃኒት በሚወሰድበት ጊዜ

የሚሶፕሮስቶል/misoprostol ክኒን ከወሰዱ በኋላ የሚከተሉት ችግሮች/ምልክቶች እንደሚያጋጥምዎ መጠበቅ ይችላሉ:

- ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ፣ ተቅማጥ፣ መደንዘዝ፣ የራስ ምታት እና ትኩሳት (ይህ በሴቶች መካከል ይለያያል)
- በግማሽ ሰዓት ውስጥ የሆድ እቃ ህመም (በአብዛኛው ከወር አበባ ከሚከሰት ህመም ጠንከር ያለ) እና ከአንድ እስከ አራት ሰዓታት በኋላ መድማት (ከወር አበባ ከሚከሰት ደም ከበድ ያለ)። ለዚህ የሚወስደው ጊዜ ገደብ መገመት አይቻልም
- ብዙጊዜ ከሁለት እስከ ስድስት ሰዓታት ባለው ጊዜ የመድማቱ ደረጃ ወደነበረው የወር አበባዊ መጠን ለመረጋጋት በግምት፤ ሌላ አስራ ስድት ሰዓታት የሚሆን ይወስዳል
- በመዳህኒት ጽንስ ማስወረድ ካካሄዱ በኋላ ያልታሰበ፤ መደበኛ ያልሆነ ወይም የመድማት ጊዜ መራዘም እስከ አራት ሳምንታት ሊቀጥል ይችላል።

## በመድሃኒት ጽንሱን ካስወረዱ በኋላ

የጽንስ ማስወረጃ መድሃኒት ከወሰዱ በኋላ የደም ምርመራ ማካሄድዎን ማረጋገጥና የአሠራር ሂደቱ ስለመጠናቀቁና ከዚህ በኋላ ጽንስ እንደሌለ ለማረጋገጥና ለመከታተል ከርስዎ ሀኪም ወይም ክሊኒክ ጋር ከሁለት እስከ ሶስት ሳምንታት ባለ ጊዜ የህክምና ቀጠሮ ማቀናጀት።

ጽንሱን ካስወረዱ በኋላ በሳምንት ጊዜ ላይ ኢንፌክሽን ብክለትን ለመቀነስ፤ መደረግ የሌለበት:

- በርስዎ ብልት ውስጥ ምንም ነገር አለማስገባት፤ ሞዴስንም ጭምር
- በብልት ወሲብ መፈጸም
- መድማቱ እስኪቆም ድረስ ማንኛውም የማፍታቻ አካል እንቅስቃሴ፤ ስፖርትን ወይም ከባድ የአካል ሥራን አለማድረግ
- ወደ ዋና መሄድ ወይም በገንዳ ውስጥ መዘፍዘፍ (ገላዎትን መታጠብ ይችላሉ)።

## በመድሃኒት ማስወረድ የሚከሰት የጎንዮሽ ጉዳትና ውስብስቦች

በመድሃኒት ማስወረጃ ከተወሰደ በኋላ የሚከሰቱ የጎንዮሽ ጉዳቶች:

- ከማህጸን መሸማቀቅ ጋር የሚፈጠር ህመም
- ያልተገመተ፤ መደበኛ ያልሆነ ወይም ለረጅም ጊዜ መድማት
- ማቅለሽለሽ
- ማስታወክ።

**በመድሃኒት ማስወረድ የሚከሰት የጤና ውስብስቦች ያልተለመዱ ናቸው፤ ነገር ግን ከዚህ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል:**

| የጤና ውስብስቦች | ምልክቶች | ህክምና |
|---|---|---|
| **የደም ስር መበጠስ /Haemorrhage** (በጣም ከባድ መድማት)<br><br>በጥቂቶች ላይ ይከሰታል ከ1,000 ሴቶች ውስጥ በአንድ ሴት | • ከሁለት ሰዓታት በላይ የሚሆን ከሁለት ትላልቅ ሞዴስ በላይ በሰዓት ውስጥ በደም መሞላት<br>• ትንሽ የሎሚ መጠን ያለው የደም መርጋት ማስተላለፍ<br>• የድካም መንፈስ ወይም እራስን መሳት | • በአስቸኳይ ለህክምና ትኩረት ይጠይቁ<br>• ለአምቡላንስ በስልክ 000 መደወል ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል መሄድ (እራስዎ መኪና አይንዱ፤ ሌላ ሰው እንዲወስድዎ ያቀናጁ)<br>• የሌላ ሰው ደም ልገሳ ያስፈልግ ይሆናል |
| **ኢንፌክሽን ብክለት**<br><br>ከ100 ሴቶች ውስጥ በአንድ ሴት ይከሰታል | ሊከሰት የሚችል:<br>• ህመም<br>• ያልተለመደ በብልት ላይ ፈሳሽ መውጣት<br>• ትኩሳት<br>• ድካም<br>• ተቅማጥ<br>• ማስታወክ | • በአስቸኳይ ለህክምና ትኩረት ይጠይቁ<br>• የርስዎን ክሊኒክ፤ አጠቃላይ ሀኪም/GP ማየት ወይም የአንቲባዮቲክ ህክምና ለማግኘት ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል መሄድ |
| **ጽንስ ሙሉ በሙሉ አለመውጣት**<br><br>ከ100 ሴቶች ውስጥ ከ2 እስከ 5 ሴቶች ላይ ይከሰታል | • የአንዳንድ ህዋሳት በማህጸናቸው ውስጥ ስለሚቆይ ተከታታይ መድማት መከሰት | • እነዚህን ለማስወገድ ከኒኖችን መድገም ወይም ቀላል የቀዶ ጥገና አሠራር ሂደት ሊያስፈልግ ይችላል |
| **የአሠራር ሂደት አለመሥራት**<br><br>ከ100 ሴቶች ውስጥ በ2 ሴቶች ላይ ይከሰታል | • ተከታታይ የሆነ የእርግዝና ምልክት ችግሮች እንደ ማቅለሽለሽና ማስታወክ | • የመድሃኒት ማስወረጃ ከኒናዎች በድጋሚ ሊወሰዱ ይችላሉ ወይም በቀዶ ጥገና ለማስወረድ ያስፈልግ ይሆናል* |

*መድሃኒቱን ከወሰዱ በኋላ ጽንስ ማስወረዱ ካልተካሄደ፤ በእርግዝናው ላይ እንዳይቀጥሉበት ይመከራሉ፤ ይህም በአንዳንድ ሁኔታውች የተወሰዱት መድሃኒቶች የሽል/ጽንሱ እድገት ላይ የተዛባ ቅርጽ እንዲኖር ምክንያት ስለሚሆን ነው።

## የሚከተሉት ካለብዎ የህክምና እርዳታ ያስፈልግዎታል:

- የሚሶፕሮስቶል/misoprostol (ሁለተኛውን ከኒና) እንደወሰዱ ከ24 ሰዓታት በኋላ ምንም ደም ካልወጣ
- በከባድ መድማት ከቀጠለ
- ከሳምንት በኋላ አሁንም የእርግዝና ምልክቶች ካለብዎ።

ይህንንም የሚከተሉትን በማነጋገር ማድረግ ይችላሉ:

- ጽንስ ማስወረዱ የተካሄደበት ክሊኒክ
- ለአጠቃላይ ሀኪም/GP
- በአቅራቢያዎ ያለ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል ይሆናል።

## የበለጠ መረጃ

ይህ የመረጃ ጽሁፍ በ Health Translations Directory ካሉት ሶስት ጽሁፎች ውስጥ አንዱ ነው። እባክዎ የሚከተሉትንም ይመልከቱ:

- ጽንስ ማስወረድ



VICTORIA State Government | Health and Human Services

- የጽንስ ማስወረድ አሠራር ሂደት- በቀዶ ጥገና

በቪክቶሪያ መንግሥት ሥልጣን ያገኘና የታተመ፤ አድራሻ 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria, የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፤ January 2019.
በድረገጽ <http://healthtranslations.vic.gov.au/> ላይ ቀርቧል።



VICTORIA State Government | Health and Human Services